Public Health
Seattle & King County

# የውሃ ኪንታሮት በሽታ (ሞለስከም ኮንተጂዮሰም)/Molluscum Contagiosum

**ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ**:

**ይህ የእውነታ ወረቀት የቀረበሎት ምክንያት:**

- ☐ **እርስዎ ወይም ልጅዎ ለሞለስከም ኮንተጂዮሰም ወይም ለውሃ ኪንታሮት በሽታ ተጋልጠው ሊሆን ስለሚችል ነው።**
- ☐ **ለመረጃ እንዲሆንዎት ብቻ ነው።**

---

## ስለውሃ ኪንታሮት ወይም ሞለስከም ኮንተጂዮሰም በሽታ አጠቃላይ መረጃ

**የውሃ ኪንታሮት በሽታ ምንድነው?**

- **የውሃ ኪንታሮት በሽታ ፓክስ በሚባል ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ የላይኛውን ቆዳ የሚያጠቃ ኢንፌክሽን ነው።**
- **በቆዳ ላይ የሚወጣ ክብ እና ህመም የሌለበት የኪንታሮት እብጠት የሚያመጣ የተለመደ የቆዳ ኢንፌክሽን ነው።**
- የውሃ ኪንታሮት ያለበት ግለሰብ በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ከማስተላለፍ ይልቅ ወደ ራሱ ሌሎች የሰውነቱ ክፍሎች ላይ የማዛመት ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

**ማን ሊይዘው ይችላል?**

- ማንኛውም ግለሰብ በውሃ ኪንታሮት በሽታ ሊያዝ ይችላል።
- እድሜያቸው ከ1-10 ዓመት ባሉ ልጆች ላይ በብዛት የተለመደ ነው።

**ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?**

- ዋናው ምልክት በቆዳ ላይ ኪንታሮት የሚመስሉ ትናንሽ የእብጠቶች እድገት ነው። እብጠቶቹ ብዙውን ጊዜ የሰው ቀለም ያላቸው፣ ነጭ፣ ቢጫ ወይም ግልጽና መሃላቸው ላይ ሰርጎድ ያሉ ናቸው።
- አብዛኛውን ጊዜ በልጆች ላይ እብጠቶቹ በፊታቸው፣ በጀርባቸው፣ በደረታቸው፣ በክንዶቻቸው እና በእግሮቻቸው ላይ ነው የሚወጡት።
- አዋቂዎች ላይ ብዙውን ጊዜ እብጠቶቹ በታችኛው የሆድ ክፍል፣ በብልቶቻቸው እና በውስጥ ጭኖቻቸው ላይ ነው የሚወጡት።
- ብዙውን ጊዜ እብጠቶቹ ህመም የላቸውም፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሊያሳክኩና እና ሊቆጡ ይችላሉ።
- እብጠቶቹ ከ2 እስከ 3 ወራት ሊቆዩ ይችላሉ።

**እንዴት ይሰራጫል?**

- ቫይረሱ በቆዳ እብጠቶች ውስጥ ይገኛል።
- እብጠቶቹ በሚቧጨሩበት ጊዜ ቫይረሱ ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች እንዲሰራጩ ያረዳል፣ በዚህም የተነሳ የእብጠቶች ቁጥር ይጨምራል።
- አንድ ሰው በቆዳው ላይ ያሉትን እብጠቶች ከነካ በኋላ እጁን ሳይታጠብ የሌላ ሰውን ቆዳ ከነካ በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል።
- እንዲሁም አልባሳት፣ ፎጣ እና ብርድ ልብስ ያሉ የግል ዕቃዎችን በመጋራት ሊሰራጭ ይችላል።

---

## ልጄ የውሃ ኪንታሮት ወይም ሞለስከም ኮንተጂዮሰም እንዳለበት እንዴት አውቃለሁ?

የጤና ባለሙያ በአንድ ሰው ቆዳ ላይ ያሉትን እብጠቶች በመመልከት የውሃ ኪንታሮት በሽታ እንዳለበት ማረጋገጥ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የእብጠቱን ናሙና ወስደው በአጉሊ መነጽር ማየት ይችላሉ።

**ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ልጅዎ የውሃ ኪንታሮት በሽታ ሊኖርበት ይችላል ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ የጤና ባለሙያዎን ያነጋግሩ። ይህ የእውነታ ወረቀት አጠቃላይ መረጃን ብቻ ነው የሚያቀርበው።**

---

## ልጄ የውሃ ኪንታሮት በሽታ ቢኖርባትስ?

**ልጅዎ የውሃ ኪንታሮት በሽታ ካለባት ወዲያውኑ ለልጅዎ እንክብካቤ ሰጪ ወይም ቅድመ ትምህርት ቤት ያሳውቁ።**

### እንዴት ህክምና ይደረግለታል?

- አብዛኛውን ጊዜ እብጠቱ ጠባሳ ሳያስቀር በራሱ ይጠፋል። አብዛኛዎቹ እብጠቶች ከ 6 እስከ 18 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ይጠፋሉ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እስከ 4 ዓመታት ሊቆይ ይችላል።
- የተበታተኑ እብጠቶች ወይም ነጠላ እብጠት ያለባቸው ልጆች መታከም አያስፈልጋቸውም።
- ስለ ሕክምና አማራጮች ከጤና ባለሙያዎት ጋር ይነጋገሩ።

### የውሃ ኪንታሮት በሽታ እንዳይሰራጭ እንዴት መርዳት እችላለሁ?

- ቫይረሱ ካለባቸው ግለሰቦች ጋር ከቆዳ ለቆዳ ንክኪ ማድረግን ይቆጠቡ።
- እንደ ፎጣ፣ ልብስ እና ሳሙና ያሉ የግል ዕቃዎችን ከመጋራት ይቆጠቡ።
- እጅዎትን በተደጋጋሚ ይታጠቡ፣ በተለይም እብጠቶችን ከነኩ በኋላ እጅዎትን ደጋግመው ይታጠቡ።
- እነዚህ እብጠቶች ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ስለሚሰራጩ፣ እብጠቶቹን ከመቧጨር ወይም ከመነካካት ይቆጠቡ።
- እብጠቶቹን ንጽህ እና ደረቅ ያድርጉ እናም በተቻለ መጠን በልብስ ወይም በፋሻ ይሸፍኑ።

---

## ልጄ ከልጆች እንክብካቤ መስጫ መአከላቱ ቀርቶ እቤት መቆየት አለበት?

**አይ እቤት መቅረት የለበትም።** ለውሃ ኪንታሮት በሽታ የተጋለጡ ልጆች ወይም ተመርምረው በሽታው እንደያዛቸው የወቁ ልጆች ወደ ሕፃናት እንክብካቤ መስጫ መሄዳቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ።

**እባክዎ የልጅዎትን የእንክብካቤ ፕሮግራም የበሽታ ፖሊሲ ይከተሉ።**

---

### የመረጃ ማጣቀሻዎች/ምንጮች:

American Academy of Pediatrics

- *Caring for our Children, Chapter 3 Health Promotion and Protection, 3.6 Management of Illness, 3.6.1 Inclusion/Exclusion Due to Illness*
- *Caring for our Children, Chapter 7 Infectious Diseases, 7.5 Skin and Mucous Membrane Infections, 7.5.7 Molluscum Contagiosum*
- *Managing Infectious Diseases in Child Care and Schools, 5th Edition. Page 127*

Centers of Disease Control & Prevention

- *Molluscum Contagiosum website https://statics.teams.cdn.office.net/evergreen-assets/safelinks/1/atp-safelinks.html*

Child Care Health Program – Public Health Seattle & King County

- *https://kingcounty.gov/depts/health/child-teen-health/child-care-health/disease-prevention.aspx. Disease Prevention Website*